# የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን
# የእምነት መግለጫ

1. ስድሳ ስድስቱን የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል ፣ ምንም ስሕተት የማይገኝበት ፣ እምነትንና ተግባርን በሚመለከት ሁሉ የመጨረሻው ሥልጣን ያለው እንደሆነ እናምናለን ።

2. በእግዚአብሔር አብ ፣ በእግዚአብሔር ወልድ ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ—አንድ አምላክ እናምናለን ።

3. በመፍጠር ሥራ ፣ ፍጥረትን በመጠበቅ ፣ በመግለጥ ፣ በመዋጀትና በመጨረሻው ፍርድ የእግዚአብሔርን ፍጹም ሥልጣንና የበላይነት እናምናለን ።

4. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም መወለዱን ፣ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ፣ ለሰው ልጆች ቤዛ ሆኖ በመስቀል ላይ መሞቱን ፣ መቀበሩን ፣ በሦስተኛው ቀን በአካል ከሙታን መነሣቱን ፣ ወደ አብ ቀኝ ማረጉንና አሁን ለእኛ እንደሚማልድ ፣ ደግሞም በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ በክብርና በግርማ እንደሚመለስ እናምናለን ።

5. ሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩን ፣ በኃጢአት መውደቁንና በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣና ፍርድ ያለበት በደለኛ መሆኑን እናምናለን ።

6. ከኃጢአት ዕዳ ፣ ኃይልና ቅጣት ሰው ሊድን የሚችለው ኃጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ምትክ ሆኖ በፈጸመው የቤዛነት ሥራ ብቻ በመሆኑ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ እንደሚጸድቅ እናምናለን ።

7. ኃጢአተኛ በኃጢአቱ ተጸጸቶ ንስሐ እንዲገባ ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ ዳግመኛ በመወለድ አዲስ ፍጥረት እንዲሆን መንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ እንደሚሠራ እናምናለን ።

8. መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ እንደሚኖር እናምናለን ። አማኙ በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቅ ኃይልን እንደሚቀበልና በልሳን እንደሚናገር ፣ በየጊዜውም በመንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላ እናምናለን ።

9. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ዛሬም ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችን ለአማኞች እያካፈለ በሙሉ ኃይልና ሥልጣን ተአምራትን በማድረግ ፣ ድውያንን በመፈወስ ፣ አጋንንትን በማውጣትና ሌሎችን አገልግሎቶችን በመፈጸም ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ለእግዚአብሔር መንግሥት መስፋት ፣ ለቤተ ክርስቲያን መታነጽ እንደሚሠራ እናምናለን ።

10. የክርስቶስ አካል በሆነች ፣ ከእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም የተወለዱ ሁሉ በሚገኙባት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን ።

11. ኃጢአተኛ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ ንስሐ በገባ ጊዜ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ መተባበሩን ለመግለጽ በአብ ፣ በወልድ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውኃ ውስጥ በመጥለቅ እንደሚጠመቅ ፣ እንዲሁም ጌታ እስኪመጣ ሞቱን ለመናገርና ከምዕመናን ጋር ያለውንኅብረት ለመግለጽ የጌታን እራት እንደሚካፈል እናምናለን ።

12. በሙታን ትንሣኤ ፣ በኃጥአን ላይ በሚደርሰው የዘላለም ፍርድና አማኞች በሚቀበሉት የዘላለም ሕይወት እናምናለን ።

# ሙሉ ወንጌል አማኞች
# ቤተ ክርስቲያን

# መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት

# መ ግ ቢ ያ

በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው የዳኑ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባሎች ያመኑትን ነገር እንዲያውቁ እና ተመሳሳይ የሆነ እምነትና መረዳት ኖሯቸው ባመኑበትና በተረዱት ጸንተው እንዲኖሩ ያስፈልጋል ። የሚድኑ ሰዎችም ስለእምነታቸው መሠረታዊ እውነቶችን እንዲያውቁ በሥርዓት መማራቸው አስፈላጊ በመሆኑ ፣ አገልጋዮች የሚጠቀሙበት የክርስትና ትምህርት ማብራሪያ መኖሩ ተገቢ ነው ። በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያኒቱ መሠረታዊ በሆኑ የክርስትና ትምህርቶች ያላትን እምነት ለተከታዩ ትውልድ እንዲተላለፍ በቅደም ተከተል በጥንቃቄ ማስፈር ያስፈልጋል ።

ስለሆነም ይህ «መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት» እንደ መመሪያ ይሆን ዘንድ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በመመሥረት በብዙ ጸሎትና ጥንቃቄ በቤተ ክርስቲያኒቱ ተዘጋጅቷል በዝግጅቱ ወቅት ቀደም ሲል የነበረው የእምነት አንቀጽ በቤተ ክርስቲያኒቱ የትምህርት ክፍል ተብራርቶ ከተጻፈ በኋላ ፡- በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፣ ወንጌላውያንና ከተለያዩ የአገልግሎት ክፍሎች በተውጣጡ በጠቅላላው ሰባ ሰባት በሚያህሉ ወንድሞችና እህቶች ታይቶ ፣ ብዙ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ባሁኑ መልኩ ተዘጋጅቶ ቀርቧል ።

ይህ የክርስትና ትምህርት መመሪያ ዋና ዋና የሆኑ የክርስትና ትምህርቶችን የያዘ ሲሆን ፡- እነዚህን ዓበይት ርእሶች ጠቅለል ባለ መልክ ለመዳሰስ እንጂ እያንዳንዱን በዝርዝር ለመግለጽ ሙከራ አያደርግም ። ስለሆነም ምዕመናን በግልም ሆነ በሕብረት የተዘረዘሩትን ርእሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማገናዘብ እንዲያጠኑ ፣ አገልጋዮችም አስፍተው እንዲያስተምሩ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች ።

ወደ እውነት ሁሉ የሚመራ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ጽሑፍ አማካይነት አገልጋዮችን ፣ ምዕመናንንና በጽሑፉ የሚጠቀሙትን ሁሉ ወደ በሰለ መረዳት ያደርሳቸው ዘንድ ቤተ ክርስቲያን ጸሎቷ ነው ።

የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች
አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን

ነሐሴ 1983 ዓ. ም.
አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ


ገጽ

I መጽሐፍ ቅዱስ - - - - - - - - - - - - - - - 11

1 ምንነቱ

1.1 የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል
1.2 የተጻፈበት መንገድ

2 ዓላማውና ሥልጣኑ/ኃይሉ

2.1 ዓላማው
2.2 ሥልጣኑ/ኃይሉ

3 የመጽሐፍ ቅዱስ ዝርዝርና መመዘኛ

3.1 የመጻሕፍቱ ዝርዝር
3.2 የመጻሕፍቱ መመዘኛ

II እግዚአብሔር - - - - - - - - - - - - - - - 16

1 የእግዚአብሔር ሕልውና

1.1 በፈጠረው ፍጥረት ይገለጻል
1.2 በሕሊና ሕግ ይታወቃል

2 የእግዚአብሔር ማንነት

2.1 መንፈስ ነው
2.2 ውሱንነት የሌለበት ነው
2.3 ከፍጥረቱ ተለይቶ በራሱ የሚኖርና ከፍጥረቱ ጋር ግንኙነት ያለው ነው
2.4 እኔነት ፡ ያለው ነው ።

3 የእግዚአብሔር ስሞች

3.1 አጠቃላይ ስሞች
3.2 ጣምራ ስሞች

4 የእግዚአብሔር ባሕርይ

4.1 ጻድቅ ፈራጅ ነው
4.2 ፍቅር ነው

4.3 እውነተኛ ነው
4.4 ቀናተኛ ነው
4.5 ሁሉን አዋቂ ነው
4.6 ቅዱስ ነው
4.7 ሁሉን ቻይ ነው
4.8 የማይለወጥ ነው
4.9 በቦታና በጊዜ ያልተወሰነ ነው
4.10 ከሁሉ በላይ ሥልጣን ያለው ነው

5 የእግዚአብሔር ሥራዎች

5.1 ፈጣሪ ነው
5.2 የፍጥረት ጠባቂና ገዥ ነው
5.3 አዳኝ ነው

6 ሥላሴ

6.1 የእግዚአብሔር አንድነት
6.2 የሥላሴ ሦስትነት
6.3 የእግዚአብሔር አንድም ሦስትምነት

7 እግዚአብሔር አብ

7.1 ማንነቱ
7.2 ሥራው

III ኢየሱስ ክርስቶስ - - - - - - - - - - - - - - - - - - 23

1 ማንነቱ

1.1 አካላዊ አቋም አለው
1.2መለኮት ነው
1.3 ልጅነቱ
1.4 ሰብዓዊነቱ

2 አገልግሎቶቹ

2.1 ሦስቱ አገልግሎቶቹ
2. የማዳን ሥራው (ምድራዊ አገልግሎቱ)
2.3 በመፈጸም ላይ ያለው አገልግሎቱ



1V መንፈስ ቅዱስ - - - - - - - - - - - - - - - - - - - 30

1 ማንነቱ

1. አካላዊ አቋም አለው
1.2 መለኮት ነው
1.3 የተጠራባቸው ምሳሌዎችና መገለጫዎች

2 የመንፈስ ቅዱስ ተግባር

2.1 በብሉይ ኪዳን
2.2 በአዲስ ኪዳን

3 የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና ሙላት
3.1 የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት
3.2 የመንፈስ ቅዱስ ሙላት

4 የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

4.1 የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ዝርዝር
4.2 የስጦታዎች አሰጣጥ
4.3 ስጦታዎቹ የሚሰጡበት ዓላማ/ምክንያት
4.4 የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አጠቃቀም

5 የመንፈስ ፍሬ

V ሰውና ኃጢአት - - - - - - - - - - - - - - - - - 39

1 ሰው

1.1 የሰው ማንነት
1.2 የሰው አፈጣጠር
1.3 የሰው ፍጥረት ይዘት
1.4 ሰው ከውድቀት በፊት
1.5 የሰው ውድቀት

2 ኃጢአት

2.1 ትርጉም
2.2 አጀማመር
2.3 የኃጢአት ሁለንተናዊነት እና እውነት
2.4 የውርስና የድርጊት ኃጢአት
2.5 የኃጢአት ውጤት
2.6 በኃጢአት ላይ የክርስቲያን አቋም

VI ደህንነት ገጽ

1 ምንነት 42

2 ዳግም ልደት

2.1 የዳግም ልደት ማግኛ መንገድ
2.2 የክርስቶስ ቤዛነት በዳግም ልደት

3 መጽደቅ

4 መቀደስ

5 መክበር

6 ልጅነት

6.1 የልጅነት ሥልጣን/በረከት
6.2 የልጅነት ተግባር

7 የእግዚአብሔር ምርጫ ፤ የሰው ነጻ ፈቃድና የደህንነት የዘላለም ዋስትና

VII ቤተ ክርስቲያን - - - - - - - - - - - - - - - - 47

1 ምንነቷ

1.1 ዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን
1.2 አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን

2 ቤተ ክርስቲያን የተገለጸችባቸው ምሳሌዎች

2.1 አዲሱ ሰው
2.2 የክርስቶስ አካል
2.3 የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
2.4 የክርስቶስ ሙሽራ

3 ዓላማና ተግባር

3.1ዓላማ
3.2 ተግባር

4 የቤተክርስቲያን ሥልጣን

4.1 በክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ላይ





4.2 በአባሎችዋ ዘንድ ቅድስናን መጠበቅ ፤ ወንጌልን መስበክ
4.3. አገልጋዮችን መሾምና መሻር

5 የአገልግሎት ስጦታዎች

5.1 ሐዋርያት
5.2 ነቢያት
5.3 ወንጌላውያን
5.4 እረኞች
5.5 አስተማሪዎች

6 አደረጃጀት

6.1 አመሠራረት
6.2 አባልነት
6.3 መስተዳደር

7 ግንኙነት

7.1 ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናትና መንፈሳዊ ድርጅቶች ጋር /
7.2 ከህብረተሰብ ጋር
7.3 ከመንግሥት ጋር

VII መላእክት - - - - - - - - - - - - - - - - - - 56

1 ማንነት

2 ዓይነታቸው

2.1 የብርሃን መላእክት
2.2 የጨለማ መላእክት

3 ሰይጣን

3.1 ማንነት
3.2 የሚጠራባቸው ስሞች
3.3 ባሕርዩና ሥራው
3.4 በሰይጣንና በመላእክቱ ላይ አማኞች ያላቸው ሥልጣን
3.5 የሰይጣንና የመላእክቱ ፍጻሜ

